# የስድስተኛው ክፍል ሜ/ጀነራል
## ምን አሉ ? (ከጌትነት)

ውሸት በአህያ አይጫንም እንዲሉ
ታሪክን በርዘው የመርዝ ብልቃጥ ሊጥሉ

የሌለን መስሏቸው ሲቀባጥሩ
ስነምግባር ለኢሕአፓ ሊያስተምሩ
ስንቱን ቀባጠሩ
አባይ ኢትዮጲያ ብላችሁ
በሌላ ስም ታጅባችሁ
ጠባችሁ ተጣባችሁ

በኮሎኒ ውሸት ታጥናችሁ
በአገር ፍርሻ ድግስ ታጅባችሁ
ምነው ዳግም አትርሱን አላችሁ

በሃምሳ ሳንቲም የዶሮ ግብር
እያስጨነቁ የትግራይን አርሶ አድር
አይ ስነምግባር
ማነው እርሱ ባርና በለስ አምጡልን ባይ
እስከ ዛሬ ሕዝብ ገዳይ
ማነው እርሱ ትምክህተኛ ወንድን ሴት ባይ
ቀሚስና ካልሽን አስቀምጦ በኋይላ መልማይ

እንድያውማ ለነገሩ
ጠርተው ላይጠሩ
በከንቱ ዳከሩ
የትግራይ ሕዝብማ
ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ
ልጆቹን ለትግል እንዳልገበረ
በኢሕአፓነት በኢዲዩነት እንዳልተሙተረ
በጅምላ መቃብር እንዳልተቀበረ
በውሸት ጥሩንባ እንዳልደንቆረ
በዋል ፈሰስ ዛሬም ቀረ

ግንባርህን አሳያቸው
ምግባርህን አስተምራቸው
ተብሎ እንዳልተነገረ
በተክለብርሃን ተጠናገረ

የአብዬን ወደ እምዬ እንዲሉ
በስነምግባር ቅሌታቸው ሳያፍሩ ተቀላቀሉ

ኢሕአፓ የለም ቀብረነዋል እያላችሁ
ምነው ታዲያ ታወሳችሁ
እያበበ እየፈካ መጣላችሁ
በሕዝባዊ አመጽ ሊያንቃችሁ !!
የወያኔ ምዝሩጥ
እንደበላህ እሩጥ!! (22.12.2017)